# ገቢያችን ህልውናችን

የገቢዎች ሚኒስቴር Ministry of Revenues

14ኛ ዓመት | ቁጥር 167 | ኅዳር 2016 ዓ.ም በነፃ የሚታደል



## በውስጥ ገፃችን

ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ / AEO/ ተጠቃሚዎች
ገጽ 3



ከፊዲፒደስ እስከ አሁኖቹ
ገጽ 5

The rights of Ethiopians returning to their homeland
ገጽ 7


### ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፡- www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፡- https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፡- https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

**በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን**

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኃላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

**በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን**

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን



የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሤ እና ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ቱሉ ግብር ከፋዮችን በመረቁበት ወቅት፤

# ያወቁ ሺዎች የተጠቀሙበት

**በሺመልስ ሲሳይ**

ለሁለተኛ ጊዜ የተዘጋጀውን በተከታታይ ትምህርት ሰነድ (ሞጁላር) የታክስ ስልጠና ተከታትለው ያጠናቀቁ ከአራት ሺ በላይ ግብር ከፋዮች በሚሊኒየም አዳራሽ ተመረቁ። ለሰልጣኞቹን የምስክር ወረቀት የሰጡት የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ ናቸው።

ሚኒስትሯ በዚሁ ጊዜ፤ ግብር ከፋዮች ለታክስ እና ተያያዥ ጉዳዮች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው በዘርፉ ላይ ዕውቀታቸው ባደገ ቁጥር ለሕግ ማስከበር ሥራ የሚወጣው ወጪ ይቀንሳል ብለዋል።

በተፈጠረላቸው ግንዛቤ ሕግን መሠረት አድርገው የሚሠሩ ግብር ከፋዮች የመኖራቸውን ያህል ከሕግ ውጪ በመሥራት ራሳቸውን ብቻ ለመጥቀም የሚፈልጉም አሉ ብለው በነዚህ ላይ እርምጃ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።

የታክስ ስርዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ቱሉ በበኩላቸው፤ ሚኒስቴሩ የሕግ ተገዢነትን ለማስፈን እያካሄደ የሚገኘው የሞጁላር ስልጠና ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።


በተዘጋጁ 13 ሞጁሎች 90 ሰዓታትን ወስዶ ለሦስት ወራት የተሰጠውን ስልጠና ተከታትለው ከተመረቁት 4ሺ 79 ግብር ከፋዮች 2ሺ 954ቱ ከአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተወጣጡ ሲሆን ቀሪዎቹ ከአዲስ አበባ ውጪ ካሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተገኙ ናቸው።

# «ሰመረ ባሪያው» ስለግብር

የሀገራችን አንዳንድ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ቁም ነገርን እያዋዙ መታረም ያለበትን ሲጠቁሙ እናያለን። ከነዚህ አንዱ በኤን ቢ ሲ ቴሌቪዥን የምንመለከተው ‹‹ሰመረ ባሪያው›› የተባለው ነው። ይህ ባለሙያ ሰሞኑን በዚሁ ቴሌቪዥን ‹‹የሳምንቱ ጨዋታ›› በተሰኘ ፕሮግራሙ በግብር ላይ ካስተላለፈው መልዕክት የተወሰነውን ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን።

‹‹መንግሥት የሚንቀሳቀሰው በግብር ገቢ ነው። መንግሥት የግብር መንግሥት ካልሆነ የሚሆነው የእርዳታ መንግሥት ነው። የእርዳታ መንግሥት ደግሞ አምባገነን ነው። እርዳታ ሰብሳቢ ብቻ ከሆነ እንደዜጋ መብት አይኖረንም። ምክንያቱም ማን በለመነው ሊጠቀም? ስለዚህ፤ ድምጻችን እንዲሰማ ቢያንስ ግብር መክፈል አለብን።

እኛ ግብር ለመክፈል ያለብንን ኃላፊነት እንዴት ነው የምንወጣው? ለብዙ ሰዎች ስለግብር ከት/ቤት ጀምሮ ትምህርት መስጠት አለበት። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋካልቲ ‹‹Public finance›› የሚባል ኮርስ እንደነበረ አውቃለሁ።




«ድምጻችን እንዲሰማ ቢያንስ ግብር መክፈል አለብን»
ሰመረ ባሪያው

‹ግብር ኃላፊነቴ ነውና መክፈል አለብኝ፤ ግዴታዬም ነው!› የሚለው ነገር ከልባችን እንዲመጣ የሚያደርገን የትምህርት ሥርዓት ያስፈልገናል። ከዚህ ይልቅ ግብርን እንደ ጠላት እና ግብር ሰብሳቢን እንደ ጠላት ሀገር

«ሰመረ ባሪያው» ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ







## ከተወቃሽነት ወደ ተመስጋኝነት

የገቢዎች ሚኒስቴር እየሠራባቸው የሚገኝባቸውን የታክስ እና የጉምሩክ ሕጎች በሚፈለገው ልክ ባይሆንም ለግብር ከፋዮቹ እያሳወቀ ተፈጻሚ ሲያደርጋቸው መቆየቱ ይታወቃል። ይህም ከጥቂት ዓመታት በፊት የግንዛቤ መስጫ መንገዶቹ ተቋሙ በሚያሳትማቸው የኅትመት ውጤቶች፣ የአየር ሰዓት በገዛባቸው የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ በተቋሙ ኢንተርኔት እና ፈቃደኛ ለሆኑ ግብር ከፋዮች በውስን የየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መድረክ አልፎ አልፎ በሚሰጥ ስልጠና ተግባራዊ ይደረግ ነበር።

እነዚህ መንገዶች ብዙም የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተከትሎ ስላልተሠራባቸው ሳቢነት የጎደላቸው እና ጥልቀት እንዲኖራቸው ተደርጎ ስላልተሠራባቸው የግብር ከፋዮች እርካታ አልነበራቸውም። ከእርካታ አለመኖር አልፎ ‹‹እናንተ መቅጣት እንጂ ማስተማርን አታስቀድሙም›› እስከማለት እንዲደርሱ አድርጓል።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን ይህን ታሪክ የሚቀይር አሠራር ተጀምሮ በመላ ኢትዮጵያ በሚገኙ የገቢዎች ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት እየተሠራበት ይገኛል። በታክስ ጉዳዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት አማካኝነት እየተሰጠ የሚገኘው ስልጠና በሰነዶች (በሞጁል) ጭምር የተደገፈ ሲሆን ይህ ሰነድ በአምስት ጥራዞች የተከፈለ ነው።

በዚህ መሠረት ሥራው ሲጀመር በአንድ ለአንድ እና የተቋማትን የስልጠና ጥያቄ ጨምሮ ለተወሰኑ ግብር ከፋዮች አጫጭር ስልጠና ሲሰጥ ነበር። ከግንቦት 2013 ጀምሮ ደግሞ 90 ሰዓታትን የሸፈነ የሦት ወራት ስልጠና ተሰጥቷል። በዚህም መሠረት 1ሺ 441 ግብር ከፋዮች በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት እስከ 2014 ዓ..ም. ሰልጥነው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል። በ2015 ዓ.ም. ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ 4ሺ 79 ግብር ከፋዮች ሰልጥነው ኅዳር 6/2016 ዓ.ም. በሚሊኒየም አዳራሽ ተመርቀዋል።

ይህን ተከትሎ ከዚህ በፊት ሚኒስቴሩ ይወቀስበት የነበረው ስለግብር በቂ ግንዛቤ የመስጠት እጥረት ቅሬታ ተቀይሮ መመስጋገን ደረጃ ተደርሷል። የሚኒስቴሩም ፍላጎት ይህ ሲሆን ወደፊት ሥራው በስፋት ቀጥሎ አንድም ግብር ከፋይ የግብር ሕጎችን ባለማወቁ ተጠያቂ የሚሆንበት ስህተት ውስጥ እንደማይገባ ማረጋገጫ ወይም ዋስትና የሚያገኝበትን ሥርዓት መዘርጋት ነው።

የሚኒስቴሩ ፍላጎት ግብር ከፋዮች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስህተት ውስጥ ገብተው ለቅጣት እንዲዳረጉ አይደለም። ሆኖም ግን ሕግን ተላልፈው ሲገኙ በየደረጃው ያለው የቅጣት ውሳኔ ያርፍባቸዋል። ከዚህ ሁሉ በፊት ግን ሕጉን አውቀው እንዲሠሩ የማስተማር ዓላማውን ወደፊትም አጠናክሮ ይቀጥላል።

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ
የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል
አቶ ሰሎሞን ዘሪሁን አባል
አቶ ሰዒድ ገልገሉ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ


ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199

## የስበጣ የግድግዳ ላይ ማስታወቂያ

**በሺመልስ ሲሳይ**




“ደረሰኝ ካልተሰጥዎ ሂሳብ አይክፈሉ” ይላል፤ ብዙ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ተለጥፎ የምናገኘው ጽሑፍ። የጽሑፉ መለጠፍ ችግር ባኖረውም “ስንቶቹ ድርጅቶች ደረሰኝ ይሰጣሉ?” የሚለው ጉዳይ ግን አነጋጋሪ ነው።

የንግድ ድርጅቶች ለደንበኞቻቸው ሽያጭ ሲፈጽሙ ደረሰኝ ስለመስጠት አለመስጠታቸው በኦሮሚያ፣ በሲዳማ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ቅኝት አድርገን ነበር።ከተሞቹም አዳማ፣ ሞያሌ፣ ያቤሎ ኮንሶ እና አርባምንጭ ናቸው።

በተደረገው ቅኝትም አብዛኛዎቹ የንግድ ድርጅቶች ለተጠቃሚው ደረሰኝ እንደማይሰጡ ተመልክተናል።በምልከታም ሆነ አንዳንድ የንግድ ድርጅት ባለቤቶችን ስናነጋግር ለዚህ ችግር ሦስት ምክንያቶችን ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያው ምክንያት፤ ሻጭ ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ደረሰኝ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን ነው።ገዢው ደረሰኝ የመጠየቅ ልምድ ኖሮት እንኳን ቢጠይቅ የግዢውን ሂደት ከማስተጓጎል ጀምሮ ዋጋ እስከ መጨመር የሚደርሱ የንግድ ድርጅቶችም እንዳሉ አስተያየታቸውን የሰጡን አንዳንድ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች ነግረውናል።በዚህም የተነሳ ተጠቃሚው ወይም ገዢው ዕቃውን ላለማጣት ወይም ዋጋ እንዳይጨመርበት በማሰብ ደረሰኝ ላለመጠየቅ ይገደዳል።

ሁለተኛው ምክንያት፤ በገቢው ዘርፍ ያሉ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ደረሰኝ የማይቆርጡ የንግድ ድርጅቶች መኖራቸውን ቢያውቁም አስተማሪ እርምጃዎችን አለመውሰዳቸው ነው።እርምጃ ቢወሰድ እንኳን አንድ ሰሞን በዘመቻ መልክ መሆኑ ለችግሩ አለመቀረፍ ተጠቃሽ ጉዳይ ነው።

በተለያዩ የምክክር መድረኮች ላይ የዘርፉ አመራሮች “ደረሰኝ በማይቆርጡ የንግድ ድርጅቶች ላይ አስተማሪ እርምጃዎችን እየወሰድን ነው” ሲሉ ይደመጡ እንጂ እውነታው ግን የተገላቢጦሽ ነው።ይህ አሁንም የዘርፉ አመራሮች በዚህ ላይ መሥራት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን ያመለክታል።

ሦስተኛው ምክንያት፤ የተጠቃሚው ደረሰኝ የመጠየቅ ልምድ ማነስ ወይም አለመኖር ነው።ይህ የሚሆነው ግንዛቤ ባለመኖር፣ “በስጠኝ አትስጠኝ” ንትርክ ውስጥ ላለመግባት ከመፈለግ፣ ከግዴለሽነት እና ከመርሳት ነው።

“ደረሰኝ ካልተሰጠዎ ሂሳብ አይከፈሉ” የሚለው ማስታወቂያ በንግድ ድርጅቶች ላይ መለጠፉ በበጎ ጎን የሚታይ ነው።ነገር ግን በጽሑፉ መሠረት መመሪያው ተግባራዊ ካልተደረገ የጽሑፉ መልዕክት ከስላቅ እና ከለበጣ የዘለለ ትርጉም አይኖረውም።

## ሰላም ፤ ስገቢ አሰባሰቡ

**በበኃይሉ ሺመልስ**

ሀገር ሰላም ስትሆን ዜጎች በነፃነት ተንቀሳቅሰው በመሥራት እራሳቸውን ጠቅመው ከሚያገኙት ገቢ ለሀገራቸው ግብር በመክፈል የሀገራቸውን ልማት እና ሰላም መደገፍ ይችላሉ።

የገቢዎች ሚኒስቴር ባለፉት ዓመታት ሀገር የተለያዩ ችግሮች ውስጥ እያለች ጭምር በከፍተኛ ትጋት የገቢ አሰባሰቡን እያሳደገ ይገኛል። በዚሁ መሰረት በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ አራት ወራት ብር 196.36 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 193.98 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 98.78 በመቶ ሰብስቧል። ከዚህ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ታክሱ ለመሰብሰብ የታቀደው 128.49 ቢሊዮን ብር ሲሆን 129.49 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱ 100.54 በመቶ ተሳክቷል።

የዚህ እቅድ መሳካት ዋና ባለቤቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሲሆኑ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአካባቢያቸው ደርሶ በነበረው ሰላም ማጣት ተስተጓጉሎ የነበረው ገቢ ወደነበረበት በመመለስ ላይ ስለሆነ ለአብነት ያህል ማንሳት አስፈልጓል። ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የመቀሌ እና የኮምቦልቻ ሲሆኑ በመንግሥት እና በተፋላሚዎች

ወደ ገጽ3 ዞሯል

## 90 በመቶዎቹ የንግድ ድርጅቶች ደረሰኝ አይቆርጡም

**በሺ.ሲ**

በቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ የንግድ ድርጅቶች 90 በመቶዎቹ ላከናወኑት ግዢ እና ለፈጸሙት አገልግሎት ደረሰኝ ሲሰጡ እንዳልነበረ አንድ ጥናት አመለከተ።

ግኝቱ ያመለከተው የንግድ ድርጅቶቹን የደረሰኝ አሰጣጥ ልምድ አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ በተካሄደው ጥናት መሆኑን የሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ሀብታሙ ታደሰ ገልጸዋል።

የጥናቱን ግኝት ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሁሉም የታክስ ማዕከላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረሰኝ በማይቆርጡ የንግድ ድርጅቶች ላይ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤



**አቶ ሀብታሙ ታደሠ**
**የሀዋሳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ**

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ደረሰኝ ባልቆረጡ 16 የንግድ ድርጅቶች ላይ እርምጃ መወሰዱን ጠቁመው ወደፊትም እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

## ደረሰኝ ያልቆረጡ 32 ድርጅቶች እርምጃ ተወሰደባቸው

**በሺ.ሲ**

በሸገር ከተማ አስተዳደር የኩራ ጂዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አለማየሁ ኃይሉ በሩብ ዓመቱ ደረሰኝ ባላቆረጡ 32 የንግድ ድርጅቶች ላይ ዕርምጃ መወሰዱን አስታወቁ። በዚህም መሠረት 1.8 ሚሊየን ብር ለመንግሥት ገቢ መደረጉን ኃላፊው ጠቁመዋል።

እርምጃው የተወሰደው ጽ/ቤቱ በሩብ ዓመቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ባካሄደው የቁጥጥር ሥራ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል።

# ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ /AEO/ ተጠቃሚዎች




ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች /Authorized Economic Operators/ ማለት በዓለም አቀፍ ገበያ የአቅርቦት ሰንሰለት ላይ ተሳትፎ ያላቸው የጉምሩክ እና የታክስ እንዲሁም ለአገሪቱ ሕጎች ታማኝ የሆኑ ናቸው። እንዲሁም በተቀመጡ አለም አቀፍ መመዘኛዎች በውስጥ አሠራር ሕግ ተገዥነት ኦዲት አልፈው በሚሰጣቸው ዕውቅና መሰረት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ፈጣን እና ቅድሚ አገልግሎት እንዲገኙ የሚመረጡ ድርጅቶች የሚታቀፉበት የአሰራር ስርዓት ነው።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 518/2014 ምዕራፍ ሦስት አንቀጽ 11 መሰረት ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሚፈቀድ ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አለ።

የዚህ ስርዓት መነሻ እ.ኤ.አ መስከረም 11/2001 በአሜሪካ የተፈጸመው ሽብር ጥቃት ነው። የአገሪቱ መንግሥት ከዚህ ጥቃት በኋላ የሚፈጠሩ የደህንነት ስጋቶችን ለመቀነስ ጉምሩክ አስተዳደር ከንግድ ማህበረሰቡ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የበኩሉን ሚና ለመወጣት እንዲችል "ሽብርተኝነትን ለመከላከል የጉምሩክ ንግድ አጋርነት" /Customs Trade Partnership Against Terrorism (C-TPAT)/" በሚል አሠራር የጀመረው ነው።

በመቀጠልም የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት / World Customs Organizations (WCO)/ እ.ኤ.አ በ2005 የገቢ እና ወጪ ዕቃዎች በጠረፍ አካባቢ በሚደረግ ፍተሻ ሳይስተጓጎል አስተማማኝ ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል "አስተማማኝ የደረጃዎች ማዕቀፍ" /Safe Framework of Standards/ የሚል አሠራር ዘርግቷል።

ይህ መስፈርት ሦስት ዋና ዋና የትብብር ምሰሶዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፡-

- በተለያዩ አገሮች የጉምሩክ አስተዳደር መካከል የሚደረግ ትብብር፤
- በጉምሩክ አስተዳደር እና በንግድ ማህበረሰብ የሚደረግ ትብብር፤
- በጉምሩክ እና በሌሎች የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ መ/ቤቶች መካከል የሚደረግ ትብብር ናቸው።

በዚህ መሰረት ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት ካስቀመጣቸው የትብብር ምሰሶዎች የሁለተኛው የትብብር ምሰሶ ማስፈጸሚያ ዋና መሳሪያ ነው።

የፕሮግራሙ ዓላማ ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የንግድ አካባቢን ደህንነት አስተማማኝ ማድረግ እና ማቀላጠፍ ነው።

**ፕሮግራሙ ለአገር ያለውን ፋይዳ**

- ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ድርጅቶች ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር በማድረግ የንግድ ደህንነትን አስተማማን ለማድረግ ያስችላል፤
- የንግድ ቅልጥፍናን በማሳደግ ገቢን ይጨምራል ኢንቨስትመንትን ያሳድጋል፤
- በራስ ተነሳሽነት ቀረጥና ታክስን በእምነት የመክፈል ባህልን ያዳብራል፤
- የንግድ ዘርፍ ለአገር ኢኮኖሚ ያለውን ሚና ለማሳደግ ዕድል ይሰጣል፤
- የዋጋ ንረትን ይቀንሳል፤
- የንግድ ማህበረሰብ አጋርነትን ያሳድጋል።

**ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም በኢትዮጵያ**

ለፕሮግራሙ በ2001 ዓ.ም በሙከራ ደረጃ 13 ድርጅቶች ተመርጠው እንዲታቀፉ በማድረግ የተጀመረ ሲሆን በጉምሩክ ኮሚሽን የአሰራር መርህ መሰረት እየተሰራበት ይገኛል።

**በፕሮግራሙ የሚሳተፉ ድርጅቶች**

በአለም አቀፍ ንግድ የአቅርቦት ሰንሰለት በዕቃዎች ዝውውር በቀጥታ ተሳትፎ ያላቸው ድርጅቶች፡-

- አስመጪዎች
- ላኪዎች
- አምራቾች
- የጉምሩክ አስተላላፊዎች
- የዕቃ አስተላላፊዎች እና ሌሎች በሎጅስቲኩ ላይ ሚና ያላቸው ናቸው።




## ባለልዩ መብት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት የመመዘኛ መስፈርቶች እና የሚገኙ ጥቅሞች

**በፕሮግራሙ ለመሳተፍ መሟላት ያለባቸው የቅድመ ኦዲት መስፈርቶች**

በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ያቀረቡ ድርጅቶች በመመዘኛ መስፈርቶች እና የአሠራር ሕግ ተገዥነት ኦዲት ከመደረጉ በፊት የሚከተሉት ሦስት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት ይጠበቅበታል።

ሀ) በጉምሩክ እና በአገር ውስጥ ገቢው የኦዲት ግኝት መጠን ከአምስት በመቶ የበለጠ መሆን የለበትም፤

ለ) የድርጅቱ የፋይናንስ እና የመጋዘን የሥራ ክፍሎች በመረጃ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ መሆን አለባቸው፤

ሐ) ድርጅቱ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ካልሆነ በስተቀር ባለፈው አንድ ዓመት ኪሳራ ያላጋጠመው መሆን አለበት፤

መ) የድርጅቱ የስጋት ደረጃ ቢያንስ መካከለኛ ደረጃ መሆን አለበት።

**በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የመመዘኛ መስፈርቶች**

በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ያቀረበ ድርጅት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን ካሟላ በኋላ በሚከተሉት ስድስት ጥቅል የመመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በሚገኝ ዝርዝር መለኪያዎች ተመዝኖ ማለፍ ይጠበቅበታል።

1. የንግድ እንቅስቃሴውን የሚመራበት ለጉምሩክ ቁጥጥር የሚያመች ዘመናዊ የሪከርድ እና የመዝገብ አያያዝ ስርዓት የሚከተል፤
2. በውል የሚገባውን ግዴታ የሚወጣ ለመሆኑ ከጉምሩክ የሚወሰነውን ዋስትና የሚያቀርብ፤
3. በጉምሩክ የተረጋገጠ መልካም ሕግ ተገዥነት ሪከርድ ያለው፤
4. ለአገር ኢኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋጽኦ፤
5. የድርጅቱ የፋይናንስ አቅም፤
6. በጉምሩክ እና በአገር ውስጥ ገቢ ያለው የሕግ ተገዥነት ታሪክ፤
7. የሎጅስቲክስ እና ሃብት አመራር ስርዓት፤
8. የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት፤
9. የደህንነት መስፈርቶች ናቸው።

አመልካች ድርጅቱ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ በመመዘኛ ነጥቦች 75 በመቶ ወይም በላይ ማስመዝገብ አለበት።

በፕሮግራሙ የታቀፉ ድርጅቶች የሚያገኙት የጉምሩክ ዋና ዋና ጥቅሞች

- በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የመስተናገድ፤
- የድህረ ክፍያ (የዱቤ) አገልግሎት፤
- በደብዳቤ ዋስትና በኮፒ ሰነድ የመስተናገድ፤
- በራሳቸው የሥራ ቦታ ወይም መጋዘን የጉምሩክ አገልግሎት የማግኘት፤
- ቀላል የጉምሩክ አገልግሎት፤
- አዳዲስ አሠራሮች ላይ ግብዓት የመስጠት፤
- በማንኛውም የጉመሩክ አገልግሎት ቅድሚያ የመስተናገድ
- በሌሎች አገልግሎት ሰጪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የቅድሚያ አገልግሎት የማግኘት ጥቅሞች ናቸው።

**የሕግ ማዕቀፎች**

- የጉምሩክ ዓዋጅ ቁጥር 859/2006
- የጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014
- መመሪያ ቁጥር 166/2012

**ምንጭ ፡-** የጉምሩክ ኮሚሽን ጥቅምት 2016 ዓ.ም. ብሮሸር

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ወርቁ


## የተመላሽ ኢትዮጵያዊያን መብት

‹‹ተመላሽ›› ማለት ከኢትዮጵያ በተለያየ መንገድ ወደ ውጪ አገር በስደት፣ በሥራ ፈቃድ ወይም በሌላ ሁኔታ ወጥተው ሲኖሩ ቆይተው በፈቃዳቸው ወይም ያለፈቃዳቸው ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ኢትዮጵያ ለመኖር የሚመለሱ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ-ኢትዮጵዊ ማለት ነው።

በዚህም መሰረት ኢትዮጵያዊ ዜጎች ወደ አገራቸው ጠቅልለው ሲመለሱ ውጪ አገር በነበሩበት ወቅት ሲጠቀሙባቸው የነበረውን የግል መገልገያዎች ይዘው እንዲመጡ ለማድረግ መንግሥት አዋጅ እና መመሪዎችን በማውጣት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 52ን ሽሮ በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 52 መሰረት "የግልና ቤት ውስጥ መገልገያ ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ መንገደኛው የሚይዘው ዕቃ ነው" በማለት ይገልጸዋል።

በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 129 (1) መሰረት ደግሞ የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት አሰጣጥን በተመለከተ የገንዘብ ሚኒስቴር ብቻ እንደሚሰጥ ደንግጓል። የገንዘብ ሚኒስቴርም ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን መመሪያ ቁጥር 923/2014ን አውጥቷል።



ለግል መገልገያ እንዲውሉ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014

የገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 2014



ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆነው የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች

የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ከእያንዳንዱ አይነት አንድ አንድ፤

መንገደኛው የሚጠቀምባቸው መድሐኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች (ለአንድ ሰው በሚያስፈልግ መጠን)፤

በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል እና ለቤተሰብ የሚያገለግሉ ልብሶች፣ ጫማዎች እና የጽዳት ዕቃዎች ናቸው።

ይህንን አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልጉ ተመላሾች በሚቀርባቸው እና እቃዎቻቸውን ባስጫኑበት ቀርበው መረጃዎችን አሟልተው አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ። ተሽከርካሪን በተመለከተ አንድ የግል አውቶሞቢል አስፈላጊው ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት በዋናው የጉምሩክ መሥሪያ ቤት በኩል ማጣራት ተደርጎበት ይፈቀዳል።

ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ-ኢትዮጵያዊያን ማቅረብ ያለባቸውን ሰነዶችና መረጃዎች በተመለከተ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 129 መሰረት የመጓጓዣ ሰነድ፣ የዋጋ ሰነድ፣ የባንክ ፈቃድ፣ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣ የስሪት አገር የምስክር ወረቀት እና ከጉምሩክ ሕግ መከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በመመሪያውያው የሚወስናቸው ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች መያያዝ እንደሚገባቸው ተዘርዝሯል።

በዚህ መሰረት ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ፣ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ውጪ አገር የኖረ እና በዚያ መቆየቱን የሚገልጽ በሚኖርበት አገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ ይገባል። እንዲሁም፤ ከአገር ሲወጡ እና ወደ አገር ሲመለሱ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ወይም አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በፓስፖርታቸው ላይ የሰፈረ ማረጋገጫ ማቅረብ ያስፈልጋል።

ተመላሾቹ የሚያጓጉዟቸው እቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ መስፈር እና መረጋገጥ አለባቸው። በተጨማሪም የሚገቡት ዕቃዎች ዝርዝር /packing list/ በአንድ ሰነድ ሊቀርብ ይገባል። የእቃዎች የዋጋ ማረጋገጫ ወይም የዋጋ መግለጫ ማቅረብ እና ዕቃው አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ያፈልጋል።

ሌላው፤ ተመላሾች ወደ ኢትዮጵያ በገቡ በስድስት ወር ውስጥ እቃዎቻቸውን አጠቃለው ማስገባት የሚጠመቅባቸው ሲሆን ከዚያ በኋላ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም።

እቃዎቻቸውን በአየር መንገድ ወይም በየብስ ማጓጓዝ የሚችሉ ሲሆን በአንዱ የማጓጓዣ ስልት ብቻ ከሆነ ሁለት ጊዜ ማጓጓዝ ይችላሉ። ሁለቱንም የማጓጓዣ መንገዶች መጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ ደግሞ በእያንዳንዱ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ መጠቀም ይችላሉ።

ተመላሾች በውጪ አገር ቆታቸው ወቅት በመሃል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ዘጠና ቀናት እና ከዚያ በላይ አገር ውስጥ ያልቆዩ መሆናቸውን በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ይገባቸዋል።

ስደተኞችን በተመለከተ ደግሞ ከስደት ተመላሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የቀረበ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

## የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ እና አወጋገድ አገልግሎት

ሀ) የሽያጭ ደረሰኝ ለማሳተም

- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (ለተመዘገበ)፤
- በንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ህጋዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ፤
- የንግድ ሥም በሚታተመው ደረሰኝ ላይ እንዲጠቀስ የሚፈልጉ የንግድ ሥም ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
- ማሳተም የሚፈረልገዉ የደረሰኝ ዓይነት ናሙና፤
- ማሳተም የሚፈልገዉ የደረሰኝ ዓይነትና ብዛት በደረሰኞች ሕትመትን መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ መሠረት ሞልቶ ማቅረብ፤
- በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን የቃል ኪዳን ውል (commitment form) መፈረም።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመሳሪያ መዝገቢያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ለ) ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም

- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤
- በንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሕጋዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ፤
- የንግድ ሥም በሚታተመው ደረሰኝ ላይ እንዲጠቀስ የሚፈልጉ የንግድ ሥም ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- በንግድ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ከሚመለከታቸው አካላት የተሰጠ ማስረጃ፤
- ማሳተም የሚፈልገው የደረሰኝ ዓይነትና ናሙና፤
- ማሳተም የሚፈለገው የደረሰኝ ዓይነትና ብዛት በደረሰኞች ህትመትን መጠየቂና መፍቀጃ ቅጽ መሰረት ሞልቶ ማቅረብ፤
- በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን የቃል-ኪዳን ውል (commitment form) መፈረም።

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**


- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመሳሪያ መዝገቢያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ሐ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለባቸው ወኪሎች ደረሰኝ ለማሳተም

- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤
- የሚታተመው ደረሰኝ ላይ የመለያ ምልክት (Logo) እንዲካተትላቸው ጥያቄ ከቀረበ ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ምልክቱ የተመዘገበበት ማስረጃ፤
- ማሳተም የሚፈልገው የደረሰኝ ዓይነትና ናሙና፤
- ማሳተም የሚፈለገው የደረሰኝ ዓይነትና ብዛት በደረሰኞች ህትመትን መጠየቂና መፍቀጃ ቅጽ መሰረት ሞልቶ ማቅረብ፤
- በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን የቃል-ኪዳን ውል (commitment form) መፈረም።



INVOICE 00001

DATE OF ISSUE: MONTH-DATE-YEAR

BILLED TO
Client Name
Street address
City, State Country
ZIP Code

FROM
YOUR COMPANY NAME
123 Your Street
City, State, Country, ZIP Code
564-555-1234
your@email.com

| DESCRIPTION | UNIT COST | QTY/HR RATE | AMOUNT |
|---|---|---|---|
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |
| Item name here | 0.00 | 1 | 0.00 |

| | |
|---|---|
| Subtotal | 0.00 |
| Discount | 0.00 |
| Tax Rate (%) | 0% |
| Tax Amount | 0.00 |
| TOTAL | $0.00 |

Terms Please pay invoice by MM/DD/YYYY. If this invoice is unpaid by the due date, a non-compounding late fee of 1.2% accrues monthly on the outstanding amount.

Template courtesy of trulysmall

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

መ) በኮምፒውተር የተዘጋጀ ደረሰኝ

- ከዋና መ/ቤት ስለመፍቀደ የተጻፈ ደብዳቤ፤
- ጥቅም ላይ የዋለውን/ የሚውለውን ከ-እስከ ማስመዝገብ፤
- በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም የማይቻልበትን አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ሠ) ደረሰኝ መጥፋትን ማስታወቅ

- ከግብር ከፋዩ ቁጥጥር ውጭ ወይም ከአቅም በላይ በሆኑ አደጋዎች /የእሳት ቃጠሎ፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ በሌባ መሰረቅ)፤
- ማስረጃ ከፖሊስ፣ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ከእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ኤጀንሲ፤
- በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በማንኛውም ጋዜጣ ወይም በመንግስት የቴላቪዥን እና/ወይም ራዲዮ ፕሮግራም ለሁለት ጊዜ ማስታወቂያ ማስነገር፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ረ) ደረሰኝ መመለስ እና አወጋገድ

- የንግድ ሥራ ሲቋረጥ ወይም የዘርፍ፣ የአድራሻ እና የሥም ለውጥ ሲደረግ የአገልግሎት መጠየቂያ ማቅረብ፤
- ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋሉ ደረሰኞች በግንባር በመቅረብ እንዲሰረዝ (Void) ማስድረግ፤
- የተሰረዘው ደረሰኝ ጥራዝ ሙሉ በሙሉ ያልተሰራበት ከሆነ ማስረከብ፣ ማስወገድ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዲደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

## ስለታክስ ማስታወቅ፣ ክፍያ ስለመቀበልና ደረሰኝ ስለመስጠት አገልግሎት

ሀ) የንግድ ትርፍ እና የኪራይ ገቢ ግብር ማስታወቅ

- በትክክል የተሞላ ዓመታዊ የግብር ማስታወቂያ ቅጽ፤
- የትርፍና ኪሳራ መግለጫና የሂሳብ ሪፖርቶች፤
- የሃብትና ዕዳ መግለጫ፤
- የኦዲት ሪፖርት ብቃት ማረጋገጫ፤
- የእርጅና ቅናሽ ስሌትና የዘመኑ የሒሳብ ሰነዶች፤
- ዊዝሆልዲንግ ዝርዝር መረጃ፤
- የዊዝሆልዲንግ ማጠቃለያ፤
- ማጠቃለያ /ኤፍ ኤም/ ሪፖርት።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ክፍያ ለመቀበልና ደረሰኝ ለመስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስታወቅ

- በትክክል የተሞላ ወርሀዊ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤
- ወርሐዊ የግብዓት ግዢ የተሞላበት ማስታወቂያ ቅፅ፤
- የወሩ የግብዓት ግዢ የሂሳብ ሰነዶች፤
- ማጠቃለያ ሪፖርት፤
- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ሐ) የተርን ኦቨር (TOT) ታክስ ማስታወቅ

- በታክስ ጊዜው በትክክል የተሞላ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤
- የታክስ ጊዜው የግብዓት ግዢ ማስታወቂያ ቅፅ የሒሳብ ሰነዶች፤
- ማጠቃለያ ሪፖርት።

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

መ) የኤክሳይዝ (Excise) ታክስ ግብር ማስታወቅ

- በትክክል የተሞላ ወርሐዊ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤
- ማጠቃለያ ሪፖርት።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ሠ) የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮና የወጪ መጋራት ግብር ማስታወቅ

- በትክክል የተሞላ ወርሐዊ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በየዓይነቱ


ለፌዲፒደ መታሰቢያ የቆመው ሀውልት፤



የመጀመሪያው አፍሪካዊ የማራቶን አሸናፊ አትሌት አበበ ቢቂላ በሮም ማራቶን በባዶ እግሩ ያሸነፈበት የ1960 ክስተት፤

## ከፌዲፒደስ እስከ አሁኖቹ

በፋርስ እና በግሪክ መካከል ከክርስቶስ ልደት በፊት በ490 ጦርነት ተካሂዶ ነበር። የዚህ ጦርነት ታሪክ ሲነሳ ደግሞ ፌዲፒደስ የተባለ የግሪክ መልእክተኛ ይታወሳል። ይህ ጦርነት በግሪኮች አሸናፊነት ሊጠናቀቅ በተቃረበበት ወቅት የፋርስ መርከብ ወደ አቴንስ አቅጣጫውን ሲቀይር ፊሊፒደስ ይመለከታል። ይህን መልካም ዜና ፌዲፒደስ ትጥቁን እና ልብሱን ሳይቀይር ከማራቶን ከተማ እስከ አቴና ያለውን 42.195 ኪሎ ሜትር (26 ማይል) ርቀት በመሮጥ ለሕዝቡ፣ "አሸንፈናል!" በማለት አብስሯል።

በዚህ መነሻነት ዛሬ የደረስንበት የሩጫ ውድድር ከ100 ሜትር ተጀምሮ ትልቁ 42 ኪሎ ሜትር ከ195 ሜትር ላይ ደርሷል። የዚህ መነሻ ደግሞ ወታደሩ ፌዲፒደስ ሲሆን ይህ ርቀት በዚያን ጊዜ የሮጠው ነው።

ዛሬ በመላው ዓለም 800 የማራቶን ውድድሮች የሚካሔዱ ሲሆን በዘመናዊ መልኩ ወደ ኦሎምፒክ የመጣው እ.ኤ.አ. በ1896 በግሪክ አቴንስ ነበር። ውድድሩ ኦሎምፒክ ውስጥ እንዲካተት ሃሳቡን ያቀረበው ሚሼል ብሬል ነበር።

ይህ ጅማሮ ደግሞ የዘመናዊው ኦሊምፒክ መስራች በሆነው በፒየር ደ ኩበርቲን እና በግሪካውያን ከፍተኛ ድጋፍ ተሰጥቶታል። ውድድሩ እስከ 1921 ድረስ ደረጃውን ሳይጠብቅ ቆይቶ ከዚያ በኋላ አሁን ያለውን ይዘት አግኝቷል። ወደ ዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮን የመጣው ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1983 ነው።

እ.ኤ.አ. መጋቢት 22/1896 በተካሔደው የመጀመሪያው የማራቶን ውድድር ቻርላዎስ ቫሲላኮስ የተባለ ሯጭ በ3 ሰዓት ከ18 ደቂቃ አሸንፏል። ሁለተኛው የማራቶን ውድድር ደግሞ ከሁለት ሳምንት በኋላ ተካሔዶ ነበር። በመቀጠል ማራቶን


ፌዲፒዳስ ዜናውን ለማብሰር የተነሳበት ማራቶን ከተማ፤

ሚያዝያ 10/1896 እ.ኤ.አ በኦሎምፒክ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ ገብቶ ስፓይሪዶን ሉዊስ የተባለ የግሪክ ውሃ ተሸካሚ በ2 ሰዓት ከ58 ደቂቃ ከ50 ሰከንድ አሸናፊ ሆኗል። ይህን ርቀት ጣሊያናዊው ስቴፋኖ ባልዲኒ በ2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ከ55 ሰከንድ አሸንፏል። ይህንኑ ውድድር ፌሊክስ ካንዲ የተባለ ሯጭ ወደ 2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ከ37 ሰከንድ ዝቅ አድርጎታል።

እንዲህ እንዲህ እያለ በየዘመናቱ ሪከርዶች ሲሻሻሉበት ቆይቶ ኢትዮጵያዊው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ በ1960 እ.ኤ.አ. ሮም ላይ በባዶ እግሩ በመሮጥ ሪከርድ በመስበር ጭምር ያሸነፈ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1964ም ቶኪዮ ኦሎምፒክ ላይ ድሉን ደግሞታል። በ1968 በሜክሲኮ በተደረገው የኦሎምፒክ ውድድር ደግሞ ማሞ ወልዴ አሸንፏል።

ማራቶን በየዓመቱ በቋሚነት ከሚካሔድባቸው ከተሞች አንዱ የሆላንዷ ሮተርዳም ነችና አትሌት በላይነህ ዴንሳሞ በ1980 ዓ.ም. ሪከርድ በመስበር ጭምር በ2፡06፡50 ገብቶባታል። ይህን ርቀት ከመካከለኛ ኪሎ ሜትሮች የጀመሩት እነአትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ እና ቀነኒሳ በቀለም ተሳትፈው በተደጋጋሚ ያሸነፉበት እና ሪከርድ የሰበሩበት ጭምር ነው።

ሴቶች በማራቶን መሳተፍ የጀመሩት ከወንዶቹ በጣም ዘግይተው ነው። እ.ኤ.አ. በ1984 የበጋ ኦሎምፒክ በአሜሪካ ሎስ አንጀለስ ሲካሔድ አሜሪካዊቷ ጆአን ቤኖይት 2 ሰዓት ከ24 ደቂቃ ከ52 ሰከንድ በመግባት አሸንፋለች። ከዚያ በኋላ ብዙዎች ወደ አሸናፊነት መጥተው የኛዎቹ ሴቶች ማለትም ፋጡማ ሮባ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ጌጤ ዋሚ፣ ቲኪ ገላና፣ እ.ኤ.አ መስከረም 24/2023 አሸናፊዋ ትዕግስት አሰፋ እና ሌሎችም በኦሎምፒክም፣ በሌሎችም ቦታዎች ለሀገራቸው እና ለራሳቸው ክብርን አስገኝተዋል።

Wikipedia Free Encyclopaedia



የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት የሴቶች ማራቶን አሸናፊ አትሌት ፋጡማ ሮባ ፤

## ኮሎኔል አብዲሳ አጋ

በወለጋ ነጆ ውስጥ የተወለደው አብዲሳ አጋ የኢትዮጵያን ጦር የተቀላቀለው በ14 ዓመቱ ሲሆን ጣልያን ኢትዮጵያን ስትወር ወረራውን ለመከላከል በሚደረግ ውጊያ ላይ መሳተፍ ጀመረ። እጅግ ዘመናዊ መሳሪያዎች ከታጠቀው የጣልያን ጦር ጋር በሚደረገው ውጊያ ላይ ባጋጠመው የመቁሰል አደጋ ህክምና ላይ ከቆየ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ ፒያሳ አካባቢ በሚገኝ ቤት በቁም እስር ላይ ነበር። በኋላ ጣልያን ኢትዮጵያን እንዲያስተዳድር በሾመችው ግራዚያኒ ላይ የመግደል ሙከራ ከተደረገ በኋላ እርሱ እና ሌሎች 37 የቁም እስረኞች ተጠርጣሪ ተብለው በከባድ ስቃይ እስር ቤት ከቆዩ በኋላ በወቅቱ የጣልያን ግዛት በነበረችው በሱማሊያ በኩል ወደ ሲሲሊ ተወስዶ በጣልያን አገር የጦር እስረኛ ተደረገ።

በእስር ቤት ጠባቂዎች ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት አብዲሳ፤ እዛው ታስሮ ከሚገኝ ዩጎዝላቪያ ምርኮኛ ሁሊዮ ጋር እቅድ በማውጣት ሁለቱም ከእስር ቤት አመለጡ። ከዚያ በኋላ ከፋሺስት ጣልያን ወታደሮች በመደበቅ እና በመሸሽ ፋንታ በአብዲሳ መሪነት እና እቅድ አውጪነት በሌሊት ታስረው ወደነበረበት እስር ቤት ተመልሰው ጠባቂዎቹ ላይ ጥቃት ፈጸሙ። በጥቃቱም የታሰሩትን እስረኞች በሙሉ ነጻ በማውጣት የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት በዓድዋ ብቻ ሳይሆን በጣሊያንም ምድር ያስመሰከረ ድንቅ ተዋጊ ነበር።

የአብዲሳ ጀግንነት በዚህ ሳያበቃ ከእስር ቤት



ያስመለጣቸውን ሰዎች በማሰባሰብ የራሱን ጦር ካደራጀ በኋላ ጣልያኖችን በገዛ አገራቸው ያንቀራጥጣቸው ገባ። ከዓድዋ ጀምሮ የኢትዮጵያውያንን ወኔ የተረዱት ጣልያኖች የአብዲሳን ጦር በፍርሃት ያዩ የነበረ ሲሆን እንደገመቱትም አልቀረ በተለያዩ ቦታዎች ተዋግቶ ብዙ ድሎችን አስመዘገበ። ይህን የተረዱት ጣልያኖች የሚያደርጉት ግራ ቢገባቸው ከበርካታ ስጦታዎች ጋር ጦሩን ይዞ የጣልያንን ሰራዊት እንዲቀላቀል መማጸን ጀምረው ነበር። ሆኖም ለፋሺስት ጦር መዋጋት አገር መክዳት እንደሆነ ነግሯቸው ትግሉን አፋፍሞ እንደቀጠለ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የአሜሪካ እና የእንግሊዝ መንግሥታት ከጀርመን ጋር ያበረችውን ጣልያንን እየተዋጉ በነበረበት ሰዓት ስለ አብዲሳ ዝና ከሰሙ በኋላ ለጦሩ የሚገባውን ድጋፍ በማድረግ የፋሺስትን ስርዓት ለማዳከም ከሚያግዙ መንገዶች አንዱ ሆኗቸው ነበር። በድጋፉ በመጠናከር ፋሺስቱን ሰራዊት ማርበድበድ የቀጠለው አብዲሳ የጣልያን ጦር ተሸንፎ ዋና ከተማዋ ሮም በአሜሪካን እና እንግሊዝ የሚመራ ጦር እጅ ስር ከወደቀች በኋላ የሚመራቸውን ከተለያዩ አገር የወጡ ወታደሮች በሙሉ ከንዳቸው ላይ የኢትዮጲያን ባንዲራ እንዲያስሩ በማድረግ እና የኢትዮጵያን ባንዲራ እያውለበለበ ሮም ከተማ ሲገባ በአለም አቀፉ ህብረት ጦር ትልቅ አቀባበል ተደረገለት። ከዚያ በኋላ ከተጨማሪ ወታደሮች ጋር በዓለም አቀፉ ህብረት ስር የሚመራ ጦር መሪ በመሆን ጀርመንን ለማሸነፍ በሚደረገው የመጨረሻ ውጊያ ላይ ተሳትፎ ግዳጁን በሚገባ በመወጣት የኢትዮጲያን ባንዲራ ከእጁ ሳይለይ በርካታ የጀርመን ከተሞችን ነጻ ማውጣት ችሎ ነበር።

ጦርነቱ ከተገባደደ በኋላም የእንግሊዝ፣ የካናዳ እና የአሜሪካ መንግሥታት ጦራቸውን ተቀላቅሎ እንዲቀጥል በርካታ ጥቅማ ጥቅሞችን አቅርበውለት ነበር። አብዲሳ ግን ኢትዮጵያ ምንም ያህል ድሃ ብትሆን ህዝቡን እና መንግሥቱን ጥሎ እንደማይሄድ በመናገር ጥያቄውን ውድቅ አደረገ። በዚህ የተናደዱ ምዕራብውያንም በፈጠራ ወንጀል ከሰው ወደ እስር ቤት አስገብተውት ነበር። በኋላም እስሩ ወደ ገንዘብ ቅጣት ተቀይሮ እንዲከፍል ከተደረገ በኋላ በክብር ወደ ሃገሩ ሊመለስ ችሏል። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ሰራዊቱን በቅንነት ያገለገለው አብዲሳ በኮኔልነት ማዕረግ የአጼ ኃይለ-ሥላሴን ልዩ ጠባቂ ጦር እየመራ ቆይቶ ንጉሱ ከስልጣን ከወረዱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

## የጣሊያን አስገባሪዎች እርምጃ

ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ በወረራ በቆየባቸው አምስት ዓመታት ከፈጸማቸው ድርጊቶች መካከል በ1930ዎቹ መጀመሪያ ግብርን እና የመደብር ግብርን ለመሰብሰብ የተጠቀማቸው ስልቶች ናቸው። ከነዚህ መካከል መርካቶ ላይ ይወስድ የነበረው እርምጃ ነው።

የጣሊያን ግብር እና የመደብር ኪራይ ሰብሳቢዎች ሊሰበስቡ ሔደው የማይከፍሉ ሲያጋጥሟቸው የመደብሮቻቸውን ጣሪያ አስነቅለው ይወስዱ ነበር። ጣሊያኖቹ ለዚህ ተግባር እንዲሆኗቸው ኢትዮጵያውያን አናጺዎችን ይዘው ነበር የሚንቀሳቀሱት።

**ምንጭ፡- አዲስ አድማስ ጋዜጣ ግንቦት 27/1997 ዓ.ም.**

# ስለታክስ ማስታወቅ፣ ክፍያ ስለመቀበልና ደረሰኝ...

ከገጽ 4 የዞረ

- የሠራተኞች ደመወዝ መክፈያ ፔይሮል (payroll)፤

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ረ) የቅድመ-ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ (Withholding) ግብር ማስታወቅ

- በታክስ ጊዜው በትክክል የተሞላ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤
- የታክስ ጊዜው ደጋፊ የሒሳብ ሰነዶች፤
- ኦርጂናል ደረሰኞች።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ሰ) የሠንጠረዥ “መ” ግብር በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው (በቋሚነት የማይሠራ) የትርፍ ድርሻ፣ ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ የስራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ፣ የመድን አረቦን፣ የመዝናኛ አገልግሎቶች/ እንዲሁም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው የእድል ሙከራ፣ ሐብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣ የካፒታል ማስተላለፍ፣ ንፋስ አመጣሽ ትርፍ፣ ያልተከፋፈለ ትርፍ፣ በቋሚነት ለሚሠራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ እና ሌሎች ገቢዎችን በተመለከተ፡-

- በየታክስ ዓይነቱ የታክስ ጊዜ በትክክል የተሞላ የታክስ ማስታወቂያ ቅፅ፤
- ግብር ማስታወቅ ሰነድ ቁጥር መስጠት፤
- ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ግብር ከፋዮች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ አያይዞ ማቅረብ፤
- ቃለ-ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት (በውልና መስረጃ) መ/ቤት የተረጋገጠ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ቀ) በውሳኔ ማስታወቂያ፣ የግብር/ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

በ) ጊዜ ስምምነት ለአንድ ጊዜ የሒሳብ ጊዜ

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

ተ) ሌሎች ክፍያዎች

- የክፍያ አገልግሎት መጠየቂያ ቅፅ መሙላት።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

ቸ) በውሳኔ ማስታወቂያ፣ የግብር/ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት ወይም ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ኀ) በግምት ስርዓት ወይም በመረጃ ግብር አወሳሰን ስርዓት የሚስተናገድ

- የንግድ ሥራ ቦታ በአካል በመገኘት መረጃ ለሚሰበስቡ የተቋሙ ሰራተኞች ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፤
- የግዥና ሽያጭ ማስረጃ፤
- በአከራይና ተከራይ መካከል የተደረገ የኪራይ ውል፤
- የድርጅቱ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ብዛትና የሚከፈላቸው የገንዘብና የዓይነት ጥቅማ ጥቅም መረጃ፤
- የመብራት፣ የውሀ፣ የስልክ፣ የነዳጅ ሌሎች ወጪዎች ማስረጃ፤
- ሌሎች ከንግድ ሥራው ጋር የተገናኙ ማስረጃዎች።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

ክፍያ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የገቢ ሒሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት

የወጪ መጋራት ክፍያን ለማከናወን

- በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (ሲፒኦ) ወይም ከ1000 ብር በታች ከሆነ ጥሬ ገንዘብ።

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ስሌት ቡድን

የኤሌክትሮኒክ ታክስ ማስታወቅ

- ስለ ኢ-ፋይሊንግ ጠቀሜታ እና ስለ አጠቃቀሙ በተቋሙ በሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ላይ መገኘት፤
- ኢ-ታክስ ስርዓት በመጠቀም ታክስ ማስታወቅ፤
- በኢ-ፋይሊንግ አጠቃቀም ረገድ ችግር ሲያጋጥም ወይም ድጋፍ ሲፈለግ መጠየቅ፤

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት (የኤሌክትሮኒክስ ፋይሊንግ ደጋፊና ክትትል ቡድን)

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- ኢ-ታክስ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት

# «ሰመረ ባሪያው» ስለ ...

ከገጽ 1 የዞረ

ጦር ማየት ተለምዷል። ግብር ጠያቂ ሲመጣ፣ ‹መጡ! መጡ!› ነው ጩኸቱ። ግብርን ለመክፈል አለርጂ የሚሆንበት ብዙ ነው። ‹ግብር አይከፍልም› ከተባለ እንደ ጀግና የሚታዩ የሚመስላቸው አሉ። ግብር መክፈል የሚያመን፣ የሚያንገሸግሸንም፣ ዕዳ የሚመስለንም ጥቂቶች አይደለንም።

ሌላው፤ ግብር መክፈል ‹እከክልኝ፣ ልከክልህ› አይደለም። ‹እኔ እዚህ ሰፈር ግብር ከፍያለሁና ለሰፈሬ አስፓልት ይሠራልኝ› ብሎ ነገር አይሠራም። ግብር ስንከፍል ግዴታችንን ተወጣን እንጂ መንግሥት በሰበሰበው ግብር የኛኑ ፍላጎት ብቻ እንዲያሟላ አይጠበቅም። መንግሥት በሰበሰበው ግብር አገልግሎቶች ያልደረሱበት ቦታዎች ይገነባል እንጂ ሁሉ ነገር ወደ አንድ ቦታ ብቻ አይሆንም። ያ ፍላጎት ያለውና ‹እኔ ዘንድ ብቻ ይገንባ› የሚል በራሱ ገንዘብ ማሠራት ይችላል። ከዚህ ውጪ መንግሥት፤ መንግሥት እንጂ ተቋራጭ አይደለምና ከ‹ምን ተጠቀምኩ?› ይልቅ ‹ሌላውስ ምን ተጠቀመ?›ን ማሰብ ይገባል።

ስንትና ስንት የሚያማርሩ ነገሮች እያሉ የምሬታችን ምንጭ ለምን ግብር ይሆናል? አሜሪካ ውስጥ አሜሪካውያን ግብራቸውን በፈቃደኝነት ከከፈሉ በኋላ ግብር ከፋይነታቸውን እና በመክፈላቸው ኩራታቸውን ለመግለጽ፣ ‹‹I am a tax payer!›› የሚል ቲሸርት ያደርጋሉ፤ ኮፍያም ያጠልቃሉ። እንዲህ ዓይነት ቲሸርት ከዚያ የሚላክላችሁ ሰዎች አድርጋችሁ የምትዞሩ ከሆነ የሀገራችንን ግብር ሳትከፍሉ ከሆነ ማድረጉ አይጠቅማችሁምና ጽሑፉን በደንብ አንብቡ።

ግብር ገማቾች ወደ ድርጅታቸው ሲሔዱ የጠላት ሀገር ወራሪ የመጣ ይመስል ‹‹መጡ!›› እየተባለ መጨነቅ የሚታይባቸው አሉ። ዓመቱን ሙሉ በአከፋፋይነት ከሚታወቅ ድርጅት ውስጥ እንደ ጥይት እሩምታ እየተፈለኩ የሚወጡ ዕቃ የጫኑ መኪኖች ሲወጡ እየታየ ገማቾች ሲመጡ መጋዘን እንደሌለው ሰው ግድግዳ ላይ አምስት ፍሬ ዘይት እና አራት ሻይ ቅጠል በማስቀመጥ የደከመች ቤት ማስመሰልና መቅለስለስ ተቀባይነት የለውም። መርካቶ ላይ እንደ ማሳያ /Show room/ በተከፈተች ሱቅ የሚሊየኖች ግብይት እየተፈጸመ ዕቃ ቅብብሉ ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ መጋዘን መሆኑ ያልታወቀ ከመሰለ የዋህነት ነው።

የ10ሺ ብር ግብር ላለመክፈል ድራማው ተአምር ነው። እንደዚህ ማምታታት እና አጭበርብሮ ለመክበር መሸዋወድ የት ለመድረስ ነው? የሙያ ሥነ-ምግባሩን ጥሶ ከሚመሰጠር ኦዲተር ጋር በማበር ለማጭበርበር መሞከር ሁለቱንም ይዞ ገደል ይከታልና ከስህተት መመለስ ይገባል።

መንግሥት ከግብር ውጪ ገንዘብ ከየት እንዲያመጣ ይፈለጋል? አፍሪካ ውስጥ’ኮ ዝቅተኛ ግብር ከሚሰበሰብባቸው ሀገራት ዋናዋ ኢትዮጵያ ናት። ስለዚህ ግብር ከማን መሰብሰብ እንደሚገባ ደጋግሞ ማሰብ ተገቢ ነው።

መንግሥት የግብር ማስከፈያ መሠረቶቹን ማስፋት አለበት። ወደ ግብር መክፈያ መረብ ውስጥ መግባት የሚገባቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ፤ ደንብ አስከባሪዎች በየጎዳናው የሚያሯሩጧቸውን ሰዎች ተንከባክቦ ወደ ታክስ ሥርዓት ማስገባት ይቻላል።

በጥቅሉ፤ መክፈል የሚገባውን በማስከፈል፣ ግብር ለመሰወር የሚሞክረውን በመቆጣጠር እና ሁሉም በሠራው ልክ እንዲከፍል በማድረግ ታክስን ፍትሐዊ ማድረግ፤ ወደ ሥርዓቱ የገባን ደግሞ ሊከፍል ሲመጣ ካለማጉላላት ማስተናገድ ይገባል።

# ሰላም ፤ ስገቢ ...

ከገጽ 2 የዞረ

መካካል በተፈረመው የሰላም ስምምነት አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል። ይህን በመመርኮዝ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሥነ-ልቦናና የቁሳቁስ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በሠራተኞች ትጋት እና በግብር ከፋዮች ወደተለመደ ተግባር መግባት የገቢ መሰብሰብ ሥራው ውጤት በማሳየት ላይ ነው።

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው የአራት ወር አፈጻጸም ቢሆንም ከሐምሌ 2015 እስከ መስከረም 30/2016 ዓ.ም. በሁለቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመረጃ ማጥራት፣ በኤሌክትሮኒክ በማሳወቅ (E-Filling) አበረታች ሥራዎች ተሠርተዋል። በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ (E-Payment) ሥርዓት በመጠቀም ከመቀሌ ቅርንጫፍ ከ36 ሚሊዮን ብር በላይ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ 491 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል።

አበረታች ሥራዎች ተሠርተዋል። በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ (E-Payment) ሥርዓት በመጠቀም ከመቀሌ ቅርንጫፍ ከ36 ሚሊዮን ብር በላይ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ 491 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል።

የአዲስ ግብር ከፋዮች ምዝገባ ላይ በመቀሌ ቅርጫፍ 145፣ በኮምቦልቻ ደግሞ 100 ግብር ከፋዮች ወደ ታክስ መረቡ ገብተዋል። በንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቅ በኩል በመቀሌ 17 በመቶ እና በኮምቦልቻ 21 በመቶ አፈጻጸም ተመዝግቧል። የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎችን በኮምቦልቻ 89.72 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያ 96 በመቶ ተከናውኗል። በታክስ ከፋዮች ከቀረቡት የታክስ ማስታወቂያዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ ውሳኔ ማውጣት በተመለከተ በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ 119 በመቶ መሸፈን ተችሏል። በአጠቃላይ ኦዲት የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባካሄደው ኦዲት ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሁም የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 15.6 ሚሊዮን ብር ማዳን ችለዋል። ከታክስ ዕዳ መቀሌ ከ80 ሚሊዮን እና ከኮምቦልቻ 81 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ አራት ወራት ከሀገር ውስጥ ታክስ መቀሌ ቅርጫፍ ከታቀደለት 653.37 ሚሊየን ብር 159.96 በመቶ በማከናወን 1045.09 ሚሊዮን ብር በላይ ሰብስቧል። በዚሁ ወቅት 577.41 ሚሊየን ብር እንዲሰበስብ የታቀደለት ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደግሞ 114.27 በመቶ በማከናወን 659.82 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ ችሏል።

ለዚህ እቅድ መሳካት የሁለቱ ቅርንጫፎች በተገኘው ሰላም በአጭር ጊዜ ውስጥ የተለመደ ተግባራቸውን ማከናወን መቻላቸው አንዱ አስተዋጽኦ ነው። ይህ አፈጻጸም ሰላም እና ፀጥታን ማስፈን ለገቢ አሰባሰቡ ያለው ሚና የጎላ መሆኑን ስለሚያሳይ ሰዎች ሠርተው ካገኙት ገቢ ላይ ግብራቸውን መክፈል እንዲችሉ ሰላም እና ፀጥታ ማስፈን የሁሉም አካላት ጥረት እና ዝግጁነት ሊኖር እንደሚገባ እናሳስባለን።

# የስበጣ የግድግዳ ሳይ ...

ከገጽ 2 የዞረ

ካለምንም ጥያቄ እና ጉትጎታ ደረሰኝ የሚሰጡ በርካታ የንግድ ድርጅቶች መኖራቸው እሙን ነው።እነዚህ ድርጅቶች ሊበረታቱ ይገባል።እነዚህ ድርጅቶች ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉት ብሎም መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያገኝ የሚችለው ሁሉም የንግድ ድርጅቶች ማንኛውንም ግብይት በደረሰኝ ብቻ ሲያከናውኑ ነው።

በአጠቃላይ ደረሰኝ የመስጠት እና የመጠየቅ ባህላችን ብዙ ይቀረዋል።ይህንንም ባህል ለማዳበር መንግሥት መሥራት ያለበት የቤት ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም የንግድ ድርጅቶች ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸውም ማወቅ ይኖርባቸዋል።

# Tips

BY SHIMELIS SISAY

## The rights of Ethiopians returning to their homeland

Returnees are people who have left Ethiopia due to emigration, work permits, or other factors and who come back to the homeland due to their willingness or unwillingness. They might be Ethiopian or born in Ethiopia.

The government has issued regulations and guidelines letting Ethiopians bring personal equipment they used abroad when they return.

The Customs proclamation no. 859/2014 has been repealed article 52 by proclamation no. 1160/2019. According to this proclamation article, 52 “personal and household effects” means that a traveler may require for his personal use and the aggregate value or quality of which does not exceed the amounts laid down in the regulation issued by the council mnisters.

The duty-free will be issued by the minister of finance according to proclamation 859/2014.

The ministry of finance has issued directive 923/2014 E.C. to permit the imported and exported goods.

**Personal equipment that are duty-free**

- Electronics goods one from each
- The medicines and medical pieces of equipment that the traveler used (For only one person’s consumption)
- The goods that are used by the family during the trip like clothes, shoes, and sanitation goods.

Those who seek this service can get the service in nearby places where they load their goods. Private autos will be allowed after paying the relevant fees and taxes if they are inspected by the Customs commission’s main office.

Returning Ethiopians and/or Ethiopians of born are expected to fulfill the necessary documents according to customs proclamation no. 859/2014 and with amended proclamation no. 1160/2019 article 129.

These documents are transport documents, price documents, bank authorization, inventory documents, origin of country, and other important documents determined by the directive that must be attached to ensure compliance with customs law.

In addition to a passport or other associated travel documents, evidence of staying abroad for atleast one year, from the Ethiopian embassy and consular office must be presented.

The commodities of the returnee have to be listed in one document and have to be verified. A packing list has to be presented in one document.

Furthermore, commodity price verification or pricing statements, as well as evidence indicating that the items have been used for a year or longer, must be provided.

Returnees must take their whole properties within six months of their arrival in Ethiopia, and requests made after that will not be accepted.

They can transport their goods by air or land and transport them twice. If they want to use both shipping methods, they can only use each one once.

Returnees must provide evidence from the ministry of foreign affairs or the relevant government body that they have not stayed in Ethiopia for ninety days or more during their stay abroad.

In the case of refugees, they must present evidence from the relevant government body that proves that they have returned from migration.

## The cooperation among the Commission and the the Organization



*Discussion among the Commission and the Organization*

The Ethiopian customs commission and the international customs organization held a conference to boost their cooperation.

Speaking at the occasion the director of institutional risk management and ethics Ms. Seraklem Abebe noted that in today’s interconnected world, where trade and commerce have no boundaries, the role of customs officials stands as a linchpin, ensuring the smooth flow of goods while upholding regulatory compliance.

Besides the active role of experts, the top management plays a pivotal role in the fight against corruption. An encouraging activity is carried out in order to comprehend the system’s vulnerabilities according to her.

Representing the international customs organization, the Rwanda Revenue Authority’s professional in charge of integrity and investigation, Ms. Peace Janet, and Mauritius revenues authority’s technical officer, internal affairs division, Ms. Naja Magwa, gave the training and shared their country’s experience.

It is reminded that the customs commission joined the World customs organization’s anti-corruption and ethics development project in 2018.

## Issue of modernizing the tax system

Ministry of revenues discussed with Bailgate’s foundation targeting to modernize the Tax system On the occasion, the state minister of revenue, Mr. Tesfaye Tullu, stated that the institution is implementing e-filling, e-payment, and e-service.

However, those activities are not being carried out as planned, and the Ministry of revenues is collaborating with Bailgate’s foundation to use new technologies, improve human resources, and improve service delivery.

Finally, an agreement has been reached between the two organizations to form a group that will begin work within the next two months.



*Discussion among the Ministry and Bailgate’s foundation*

## The World bank’s willingness to support the sevenue sector



The Ministry of revenues and the world bank discussed ways to upsurge the revenue sector.

Minister of revenues, Mrs. Aynalem Nigussie said that the world bank is willing to support the country’s effort to cover the national disbursement with national income. To achieve this super-ambitious plan building a modern tax management system is mandatory according to her.

State minister of revenues Mr. Tesfaye Tullu on his side said that the world bank is one of the partners that is working to support the revenues sector.

The institution aimed to support the sector on policy issues, boosting the domestic tax, and improving service delivery and technology according to him.

The document pertaining to the issue was presented by Mr.Rajul Awasti who represented the World Bank delegation.

In his presentation, he stated that the World bank would keep supporting the country by enhancing its technology capabilities in order to boost the amount of money collected from voluntary taxpayers.

It is reminded that the minister of revenues Mrs. Aynalem Nigussie discussed with the World bank country director Mr. Ousman Dine with the same issue.



# ሕግ-ግብር

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

## የቻይናው ድርጅት ሴራ በኢትዮጵያ

ዋና መሥሪያ ቤቱ ቻይና የሆነው «ቻይና ፓዎር ኢኩፐመንትና ቴክኖሎጂ» የተሰኘ ድርጅት ሰኔ 25/2005 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተመዘገበ ነው። ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ጨረታ ባሸነፈባቸው የሥራ ዘርፎች ላይ ለመሥራት የሚያስችል የንግድ ሥራ ዘርፍ አውጥቷል። ሚስተር ሊዮ ኩያንግ ከ2014 እስከ 2016 እና ሚስተር ቺን ቻሆ ደግሞ ከ2017 እስከ 2018 እ.ኤ.አ ድረስ በዋና ሥራ አስኪያጅነት አገልግለዋል።

ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ፓዎር ኮርፖሬሽን እና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር ቻይና በሚገኘው ዋና መ/ቤቱ (ቻይና ኤሌክትሪክ ፓዎር ኢኩፐመንት እና ቴክኖሎጂ ሊሚትድ ካምፓኒ) ዋና መ/ቤት ስም በተለያየ ጊዜ የስምንት ፕሮጀክቶች ኢንጂነሪንግ የግዥ እና የግንባታ ሥራዎችን አጠናቆ ለማስረከብ የውል ስምምነቶችን አድርጓል።

- ከዚህም ሥራውን ሠርቶ ካገኘው ገቢ ውስጥ ከውጪ አገር ዕቃ አቅርቦት ያገኘውን 1 ነጥብ 8 ቢሊየን ብር፤
- ከሲቪል ሥራዎች ያገኘውን 383 ነጥብ 7 ሚሊየን ብር፤
- ከዲዛይንና ኢንስታሌሽን ሥራ ያገኘውን 88 ነጥብ 6 ሚሊየን ብር፤
- እንዲሁም ከትራንስፖርት አገልግሎት ያገኘውን 200 ሚሊየን 145 ሺህ ብር በላይ ገቢ በመደበቅ በሒሳብ መግለጫ ለግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት አላሳወቀም።

ይህ ድርጅት ትክክለኛ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ካልተሰማሩ እና ዕቃ ሳይሆን ደረሰኝ በመሸጥ ከተለዩ ድርጅቶች የተቆረጡ ደረሰኞችን አቅርቧል። አጠቃላይ የያዙት የገንዘብ መጠን 28 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር ግምት ያላቸው ሀሰተኛ/የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ተጠቅሟል። እንዲሁም ትክክለኛ የአገር ውስጥ ግዥ ሳይፈጽም እንደፈጸመ በማስመሰል በሒሳብ መዝገቡ ውስጥ በማካተት ወጪውን በማናር ግብር የሚከፈልበትን ትክክለኛ ገቢ ደብቋል። በአጠቃላይ ከ2014 እስከ 2018 እ.ኤ.አ ባሉት የግብር ዓመታት መክፈል የሚገባውን ከ8 ነጥብ 8 ሚሊየን ብር በላይ ፍሬ ንግድ ትርፍ ግብር ሰውሯል።

ድርጅቱ ከነሐሴ 1/2005 ዓ.ም ጀምሮ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ቢሆንም እ.ኤ.አ. ከ2016 እስከ 2018 ባሉት የግብር ዘመናት መክፈል የሚገባውን ትክክለኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ አልከፈለም። ከዚህ ሌላ ሃሰተኛ/የተጭበረበሩ ደረሰኞችን እና አሳሳች የንግድ ትርፍ ግብር መግለጫ አቅርቧል። ኢትዮጵያ ውስጥ አከናውኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍልበት ገቢ ካገኘባቸው ኢትዮጵያ እና ኬንያ በኤሌክትሪክ የማስተላለፍ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ሥራ ከሚሠራባቸው ሁለት ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ሥራ ውስጥ ለዲዛይን፣ ለተከላ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ከአሠሪዎቹ ከተከፈለው ክፍያ ውስጥ በኢትዮጵያ ብር የሚከፈለውን ብቻ በማሳወቅ በቻይና ዩዋን ለዋናው መሥሪያ ቤት የተከፈለው በኢትዮጵያ ብር ተቀይሮ 159 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ሽያጭ/ገቢ አላሳወቀም። በመሆኑም ድርጅቱ አጠቃላይ ከ8 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር በላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰውሯል።

በዚያ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት እና እንዲካካስለት ደብዳቤ በመጻፍ የጠየቀ በመሆኑ በፈጸመው የንግድ ስወራ ወንጀል ተከሷል።

ሁለቱ ሥራ አስኪያጆች በዚህ ጊዜ ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ቁጥጥር ማድረግ ሲገባቸው ከሥራ አሥኪያጅ የሚጠበቀውን ግዴታ ባለመወጣት በፈጸሙት የንግድ ትርፍ ግብር ስወራ ወንጀል ተከሰዋል።

ተከሳሽ ድርጅቱ ከህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ ከውጪ አቅርቦት የተገኘ ወደ 1 ቢሊየን 25 ሚሊየን ብር አካባቢ ገቢ ሪፖርት ማድረግ ቢኖርበትም አላደረገም።

ከህዳሴ ግድብ ሰብስቴሽን ፕሮጀክት ወደ 510 ሚሊየን ብር፣ ከአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ሶስተኛው ክፍል 25 ሚሊየን ብር፣ ከአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ከኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ላይ 83 ሚሊየን ብር፣ ከኢትዮ-ኬንያ ሎት 2 ወደ 56 ሚሊየን ብር፣ ከኢትዮ-ኬንያ ሎት 3 ወደ 57 ሚሊየን 476ሺ ብር በታክስ ሕግ 979/2008 መሰረት ለገቢዎች የሒሳብ ማሳወቂያ ላይ አካቶ ማቅረብ ሲገባው አላካተተም።

እንዲሁም ከዲዛይንና ኢንስታሌሽን ሥራ ያገኘው ገቢ ዕቃ ሳይሆን ደረሰኝ ብቻ ይሸጣሉ ተብለው በገቢዎች ሚኒስቴር ከተለዩ ድርጅቶች ሕገ-ወጥ የግዥ ደረሰኞችን አቅርቦ እያለ «ግዥ ፈጽሜያለሁና ተቀናሽ ይደረግልኛል» በማለት የተሳሳተ ማስረጃ አቅርቧል።

አጠቃላይ የንግድ ትርፍ ግብር ያልከፈለው 837 ነጥብ 2 ሚሊየን፣ ወለድ 833 ነጥብ 09 ሚሊየን፣ መቀጫ 1 ነጥብ 17 ቢሊየን፤ በድምሩ 2 ነጥብ 8 ቢሊየን ብር አልከፈለም።

ከዚህም በተጨማሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ 8 ነጥብ 3 ሚሊየን፣ ወለድ 8 ነጥብ 3 ሚሊየን፣ መቀጫ 9 ነጥብ 7 ሚሊየን ብር በኦዲት ተገኝቶበታል።

በመሆኑም ድርጅቱ ከ2014 እስከ 2018 እ.ኤ.አ ማሳወቅ የነበረበት 29.8 ቢሊየን ብር ቢሆንም ያሳወቀው 6.4 ቢሊየን ብር ብቻ መሆኑ ታውቋል።

የንግድ ትርፍ ፍሬ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ስወራ ወንጀል በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 125 (1) ከ100ሺ እስከ 200ሺ ብር እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

የሐሰት ወይም አሳሳች የንግድ ትርፍ ግብር መግለጫ እና የተጭበረበሩ ሰነዶች ማቅረብ ወንጀል በአዋጁ አንቀጽ 118 (1) "ለ" እና "ሐ" ስር ከ50ሺ እስከ 100ሺ ብር መቀጮ እና ከሦስት ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

እንዲሁም ሕገ-ወጥ የሆነ ተመላሽ መጠየቅ እና ከተገቢው በላይ ማካካሻን መጠየቅ በአዋጁ አንቀጽ 121 (1) ስር ከ50ሺ ብር እና ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

መንግሥት ከድርጊቱ ያጣውን ገንዘብ መጠን በመመልከት እና በአገር ኢኮኖሚ ላይ ያደረሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ከግምት በማስገባት ፍርድ ቤት የወንጀሉን ደረጃ ከፍተኛ ነው ሲል መድቦታል።

በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በመሆኑ እና በሕጉ ልዩ ክፍል ማለትም ጥፋተኛ በተባለበት አዋጅ ላይ ለጥፋቱ የተቀመጠው የ17 ዓመት ቅጣት በብር መቀጮ ተቀይሮ 375ሺ ብር ቅጣት እንዲሁም በገንዘብ የሚያስቀጣው 350ሺ ብር እንዲቀጣ ተወስኗል።

ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ250ሺ ብር እንዲቀጡ ወስኗል።

## «ይግባኝ፤ መብትም፣ ፍትህም ነው!»

የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዳዊት ገ/መስቀልን "የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 የተለያዩ ድንጋጌዎችን ተላልፈሃል" በማለት ስድስት የተለያዩ ክሶችን አቅርቦበታል።

በ1ኛው ክስ "ፍሬ የንግድ ትርፍ ግብር ሰውረሃል።" የሚል ሲሆን ይህም የአዋጁን አንቀጽ 125/1 "ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከ100 ሺ እስከ 200 ሺ ብር እና ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።" በማለት የተመለከተውን ተላልፏል።

በመሆኑም መክፈል የሚገባውን ትክክለኛ ግብር ላለመክፈል በማሰብ ከሽያጭ ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ በመቀነስ በቀሪ ደረሰኝ ላይ አነስተኛ የገንዘብ መጠን እንዳገኘ ገልጿል። ገቢውን በመደበቅ እና ትክክለኛ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ካልተሰማሩ ደረሰኝ ብቻ ከሚሸጡ ምንም ሽያጭ እንዳላከናወኑ ከገለጹ ግብር ከፋዮች የተቆረጡ ደረሰኞችን አቅርቧል። የግዥ ደረሰኞቹ ላይ ቁጥር በመጨመር ማጭበርበር በተፈጸመባቸው አጠቃላይ 207 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ባላቸው 94 ሐሰተኛ ደረሰኞች ግዥ ሳይፈጽም "ገዝቻለሁ" ብሏል። ወጪውን በማናርም ግብር የሚከፈልበትን ትክክለኛ ገቢ በመደበቅ የንግድ ትርፍ ግብር ሰውሯል።

ሁለተኛው ክስ "የሐሰት ወይም አሳሳች የንግድ ትርፍ ግብር መረጃ ማቅረብ" የሚል ሲሆን ይህም የአዋጁን አንቀጽ 118/1/ (ሀ) "ለግብር ባለሥልጣኑ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ፤"

ለ) "ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ የሚገባን መግለጫ አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ያለበቂ ምክንያት ያስቀረ እንደሆነ፤"

ሐ) "ለባለሥልጣኑ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ በአጠቃላይ ከ50 ሺ እስከ 100 ሺ ብር እና ከ3 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" በሚል የተመለከተውን ተላልፏል።

በ3ኛው ክስ "የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰውረሃል።" የተባለ ሲሆን ይህም የአዋጁን አንቀጽ 125/1 "ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣ የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከ100 ሺ እስከ 200 ሺ ብር እና ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" በሚል የተመለከተውን ተላልፏል።

በ4ኛው ክስ "የሐሰት ተጨማሪ እሴት ታክስ መረጃ አቅርበሃል።" የተባለ ሲሆን ይህም በአዋጁ አንቀጽ 118/1/ (ሀ) "ለባለሥልጣኑ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ፤" ወይም፤

ለ) "ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ የሚገባን መግለጫ አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ያለበቂ ምክንያት ያስቀረ እንደሆነ፤"

ሐ) "ለባለሥልጣኑ የተጭበረበሩ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ፤ ከ50 ሺ እስከ 100 ሺ ብር እና 3 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" በሚል የተመለከተውን ተላልፏል።

በዚህ ክስ ላይ "ከላይ በ1ኛ ክስ በተጠቀሱት ሐሰተኛ ደረሰኞች በመጠቀም መክፈል የሚገባውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አልከፈለም፣ ለግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቱ በማጋነን ሐሰተኛ መረጃ በማቅረቡ የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ አቅርቧል።" ይላል።

በ5ኛው ክስ "የሽያጭ ዋጋን በማሳነስ አቅርበሃል።" ተብሏል ይህም የአዋጁን አንቀጽ 120 (3) የተመለከተውን "የሽያጩ ትክክለኛ ዋጋ ከ100 ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ በደረሰኞቹ ላይ ከተመለከቱት ከፍተኛው የገንዘብ መጠን እና ከ7 ዓመት እስከ 10 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" የሚለውን ተላልፏል።

በዚህ ክስ ላይ "በ1ኛ ክስ የተጠቀሱት ሐሰተኛ ደረሰኞች በመጠቀም በአንድ ግብይት የተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽጭ ዋጋን በማሳነስ ወንጀል ፈጽሟል።" የሚል ነው።

በስድስተኛው ክስ "የተጭበረበሩ ወይም ህገ-ወጥ ደረሰኞች ተጠቅመሃል" ይላል። ይህ ደግሞ የአዋጁን አንቀጽ 119/1/ (ለ) "የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ከተጠቀመ 100ሺ ብር ቅጣት እና ከ7 ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለውን ተላልፏል።

እንዲሁም አንቀጽ 119/2/ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን በመጠቀም የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ከ100 ሺ ብር የሚበልጥ እንደሆነ ከገንዘቡ ጥቅም ጋር እኩል የሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከ10 ዓመት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" የሚለውን ተላልፏል።

በዚህም ክስ ላይ "ከላይ በ1ኛ ክስ በተጠቀሱት ሐሰተኛ ደረሰኞች በመጠቀም ግዥ ሳይፈጽም ገዝቻለሁ" እና «የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ አቅርቧል" በማለት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሶታል።

ፍርድ ቤቱ ከሳሽ እና ተከሳሽን ካከራከረ እና ማስረጃዎቹን ከሰማ በኋላ በ1ኛ፣ 3ኛ እና 6ኛ ክሶች ላይ ዳዊት ገ/መስቀል እንዲከላከል፤ በ2ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክሶች ላይ ደግሞ መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ እንዲሰናበት በማለት ብይን ተጥቷል።

በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ዳዊት ገ/መስቀል እንዲከላከል በተባለባቸው ሦስት ክሶች መከላከያ እንደሌለው የገለጸ በመሆኑ ጥፋተኛ በማለት በ8 ዓመት ከ8 ወር ጽኑ እስራት እና 110ሺ ብር እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል።

ሆኖም የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል።

ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን እና ተከሳሽን ካከራከረ በኋላ "ዳዊት ገ/መስቀል በስድስቱም ክሶች ጥፋተኛ ነው።" ብሎ በ14 ዓመት ጽኑ እስራት እና 205ሺ ብር እንዲቀጣ ወስኖበታል።

ዳዊት ገ/መስቀል በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም "የተከሰስሁባቸው ክሶች (ድንጋጌዎች) ግባቸው ታክስ ስወራ ነው። "ታክስ ሰውሯል" ተብሎ ከተጠየቀ በኋላ ተመልሶ "በተደጋጋሚ አሳሳች መረጃ አቅርቧል" ተብሎ መከሰሱ ተገቢነት የለውም። ምክንያቱም፤ ከወንጀል ሕግ አንጻር 2ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክሶች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ድንጋጌዎች ስላልሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 (3) መሰረት 1ኛ፣ 3ኛ እና 6ኛ ክሶች መጠቃለላቸው ተገቢ ነው። ይህም በሰበር መዝገብ ቁጥር 104637 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል። በመሆኑም «የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮልኝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልኝ" በማለት አቅርቧል።

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ስድስቱም ክሶች ላይ በዳዊት ገ/መስቀል የተጠቀሱትን 2ኛ ክስ "የሐሰት ወይም አሳሳች የንግድ ትርፍ ግብር መረጃ ማቅረብ"፣ በ4ኛ ክስ "የሐሰት ተጨማሪ ዕሴት ታክስ መረጃ ማቅረብ" እና በ5ኛ ክስ "የሽያጭ ዋጋን በማሳነስ" በፈጸመው ወንጀል እና 1ኛ ክስ "የንግድ ትርፍ ፍሬ ግብር የሰወረ በመሆኑ"፣ በ3ኛ ክስ "በፈጸመው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ስወራ" እና 6ኛ ክስ "በፈጸመው የተጭበረበሩ ወይም ህገ-ወጥ ደረሰኞች መጠቀም" ወንጀል መፈጸሙን የሚገልጹ ናቸው።

ዳዊት ገ/መስቀል በግልጽ ዘርዝሮ ባስቀመጣቸው ተግባራት እና "ተከላከል" ተብሎ በተቀጣባቸው ድንጋጌዎች አለአግባብ በተደራራቢነት እንዲቀጣ መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል። ስለሆነም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳዊት ገ/መስቀልን በስድስቱም ክሶች "ጥፋተኛ" በማለት በ14 ዓመት ጽኑ እስራት እና 205 ሺህ ብር እንዲቀጣ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባዋል ብሏል።

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በበኩሉ "በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ከአንቀጽ 116 እስከ 133 የተደነገጉት የተለያዩ የወንጀል ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ የታክስ ስወራ እና ማጭበርበርን መከላከል ነው። እነዚህ የወንጀል ድንጋጌዎች የየራሳቸው የተለየ አላማ እና ግብ የሚኖራቸው እንደሆነ እና የታክስ ሥርዓቱን ድርጊቶችን ልዩ ባህሪ እና ሕግ አውጪው ሊያሳካ ያሰበውን ግብ ከግምት ያላስገባ ነው።" ብሏል።

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳዊት ገ/መስቀል ላይ የቀረቡትን 2ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክሶችን በ1ኛ 3ኛ እና 6ኛ ክሶች ስር በማጠቃለል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል።

በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የ14 ዓመት ጽኑ እስራት እና 205ሺ ብር ውሳኔ በመሻር የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን የ8 ዓመት ጽኑ እስራት እና 110ሺ ብር መቀጮ ውሳኔ አጽንቷል።

### የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

### እሴቶች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)